# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 37 ጥር 21 2001 ዓ.ም


አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

"...እያንዳንዱ እነሱ በስልጣን የሚቆዩበት ቀን ለአገራችን፤ ለሕዝቡዋ፤ ለመጪው ትውልድ በጣም አደገኛ የሆነ ሁኔታን የሚፈጥርና መመለሻ የሌለው ማጥ ውስጥ የሚከተን፤ እዚያ ከመድረሳችን በፊት በአስቸኩዋይ ይህን መንግስት ማንኛውንም መንገድ ተጠቅመን ማስወገድ አለብን .... "

## ምን ላይ ስንደርስ ነው በቃን የምንለው?

የግንቦት 7 ንቅናቄ በዳላስ በጠራው ህዝባዊ ስብሰባ ላይ
ዶ/ር ብርሀኑ ነጋ ያደረጉት ንግግር
የመጀመሪያ ክፍል

(በገፅ 3 ላይ ይመልከቱ)

### ማስታወቂያ

ዛሬ በግንቦት7 ንቅናቄ ውስጥ የተሰባሰብነው ግለሰቦች ሃገራችን ወደሌላ የአመጽ አዙሪት እንዳትገባ ከምር ተጨንቀን፣ አንቸኩል! ለወያኔ እድል እንስጠው፤ ግድ የላችሁም እነዚህ ሰዎች የእዚችው ሃገር ዜጎች ናቸው ውለው አድረው ለሀገራችን በጎ መመኘታቸው አይቀረም ብለን ብዙዎች እስከሚታዘቡን መሟገታችንን ----ያውቃሉ?

ሽህ ግዜ ቀናውን፣ ሽህ ግዜ የሰላሙን መንገድ ብንመኘው፣ ሽህ ግዜ እረ ተው፣ ይህች ሃገርና ሁላችንም በጥፋት አዙሪት ውስጥ መድፈቁ ይብቃን ብለን ብንማጸን፤ ከእዚህም አልፎ ተርፎ በታሪካችን አድርገን የማናውቀውን፣ ለሰላም ካለን ጽኑ ፍላጎት ተነስተን፣ በሃገራችን ላይ የተሰራውን በደል ወደ ጎን አድርገን፣ በነጻነታችን ተደራድረን ለእረቅ ለስምምነት ጉሮሯችን እስኪደርቅ በመወትወታችን ፤ ከመለስ ዜናዊና ከጓደኞቹ ያገኘነው ምላሽ፣ እየገዘፈ የሚሄድ ዘረኛነት እብሪትና ንቀት እንደሆነ እርስዎስ ቢሆን ሳይታዘቡት አይቀርም፡፡

እነዚህ ዘረኛ እብሪተኞች ትእግስታችንና ተማጽኗችንን ከፍርሀት የሚቆጥር፣ ያለእኛ ደፋር የለም አንዲሉ አድርጎ የሚያይ በባሩድ ሽታ የሰከረ ህሊና ያላቸው መሆናቸውን እርስዎም እንደኛ ሳይረዱት አይቀርም፡፡

በተደጋጋሚ ኢትዮጵያዊ ስሜት ያላቸውን ዜጎች ማሰቃየት ማዋረድና ማዋከብ ስራ ብለው ተያይዘውታል፡፡ የቅረቡ ሰለባቸው ቴዲ አፍሮ የሆነበት ምክንያት የሚነሳው ከእዚሁ ለኢትዮጵያ ካላቸው ጥላቻ ነው፡፡ በልምና በምልጃ ስለሰላምና እርቅ በመስበክ የለየላቸው አረመኔዎችን ወደ ቀና ጎዳና መመለስ ይቻላል ብለን እኛ በግነብት ሰባት ውስጥ የተሰባሰብን ወገኖዎችዎ አናምንም፡፡ ይህንን እምነታችንን የሚጋሩ ከሆነ! ይነሱ ይቁሙ እኔንም በቃኝ ውርደት ብለው ከቆሙቱ ጎን ቁጠሩኝ ይበሉ፡፡

የግንቦት7 ንቅናቄን ሁለ ገብ ትግል ይደግፉ፡፡ ለእዚህ ትግል ማራመጃ ግንቦት ሰባት ይሆን ዘንድ ግንቦት 7 የጀመረውን የገንዝብ ማሰባሰብ ስራ ያግዙ፡፡ ሌላውም እንዲተባበር ያስተባብሩ፡፡

**ግንቦት 7 ለፍህ ለነጻነትና ለዴሞክራሲ ንቅናቄ**

ግዜ
ግንቦት 7 ዜና

## ታላቅ ህዝባዊ ስብሰባ በዳላስ

ግንቦት 7 ለፍትህ ለነፃነትና ለዲሞክራሲ ንቅናቄ በአሜሪካን አገር በዳላስ ከተማ ላይ ከትናንት በስቲያ ጥር 17 ቀን 2001 ዓም በኳሊቲ ሆቴል የጠራው ስብሰባ እጅግ በርካታ ኢትዮጵያዊያኖች በተገኙበት በተሳካ ሁኔታ እንደተካሄደ የግንቦት 7 ዘጋቢ ከስፍራው ከላከልን ሪፖርት ለመረዳት ተችሎአል።

የቀድሞ የቅንጅት አመራር ከእስር ከተፈቱ ቦኋላ በሰሜን አሜሪካ እድርገውት ከነበረው ጉብኝት ወቅት ወዲህ በከተማው እስከዛሬ ከተደረጉት የፖለቲካ ስብሰባዎች ሁሉ የላቀ የህዝብ ብዛት ተገኝቶበታል የተባለው ይህ ስብሰባ በጋለ የአገር ፍቅር ስሜት የተካሄደ እንደነበረና በጾታ፤ በዕድሜና በፖለቲካ አመለካከት የሁሉንም የህብረተሰባችንን ተዋፅኦ የሚያንጸባርቅ ተሳታፊ እንደተገኘበት ለማወቅ ተችሎአል።

(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ወያኔ የለኮሰው የሀይማኖት ግጭት

የግንቦት 7ድምጽ፤ ወያኔ የሀይማኖት ግጭትን ለማስነሳት በየቤተክርስቲያን እና መስጊዶች በሰገሰጋቸው ካድሬዎች እየቀሰቀሰ እና የየእምነቱን ቅዱሳን የሚያንቋሽሹ ፖስተሮችን በመለጠፍ ግጭት እንዲነሳ መሰሪ ተልእኮውን እያራመደ እና ዝግጅቱን እያጠናቀቀ መሆኑን በዘገበበት ከአንድ ሳምንት ባልበለከጠ ጊዜ ውስጥ በጎንደር ከተማ ሁከት ተነስቶ የአንድ ሰው ህይወት ማለፉ ተዘገበ።ለሁከቱ መነሻ የሆነው በጎንደር ከተማ ባለፈው ሳምንት የጥምቀት በአል በተከበርበት ወቅት የማርያም ታቦት የሚያድርበትን ቦታ ወያኔ ሆን ብሎ ለቅዱስ ቁርአን ትምህርት ቤት በመሰጠቱ እና የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ታቦቱን አጅበው በስፍራው ሲደረሱ በተነሳው የቦታው የይገባኛል ግጭት እንደሆነ የአይን እማኞች ተናግረዋል።ይህ በዚህ ሳያበቃ በተመሳሳይ ሁኔታ በከተማው ውስጥ ቀደም ሲል የቅዱስ ገብርኤል ታቦት ማድሪያ የነበረን ስፍራ ለመስጊድ ግንባታ መሰጠቱ ተያይዞ ታውቋል። በጎንደር ካልጠፋ ቦታ ታቦታቱ የሚያድሩበትን ቦታ እያደኑ ለመስጊድ ግንባታ መስጠት እውነት ሙስሊም ወገኖቻችንን ለመጠቀም ታስቦ ሳይሆን ወያኔ በሀገሪቱ እየለኮሰ ያለው የሃይማኖት ግጭት ቀጣይ ክፍል ነው ብለው የአካባቢው ነዋሪዎች በፀፀት ይናገራሉ።

(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ለካናዳ መንግስት የቀረበ አፋጣኝ ጥሪ

የካናዳ መንግስት የመለስ ዜናዊን ዘረኛ እና ፋሺታዊ አገዛዝ በይፋ እንዲያወግዝ ተጠየቀ።የካናዳ ፓርላማ አባል የተከበሩ ማሪያ ሚና ለካናዳ ጠቅላይ ሚኒስትር ስቴፈን ሀርፐር በላኩት ደብዳቤ እንደገለጹት የኢትዮጵያ ህዝብ፤ ተቃዋሚዎችን ባለ በልለ ሀይሉ ለማጥፍት ቆርጦ ከተነሳ እና የሰብአዊ መብት ተንከባካቢ ድርጅቶችን እንቅስቃሴ ህገ ወጥ ካደረገ ጨቋኝ አገዛዝ ጋር እየታገለ ነው ብለዋል። ማሪያ ሚና ለጠቅላይ ሚኒስሩ በጻፉት ደብዳቤ በቅርቡ የወያኔ መንግስት ሆን ብሎ የሲቪል ማህበረሰቡን ለማጥፋት ያጸደቀው ህግ በዋናነት ሁለት ቡድኖችን ታሳቢ ያደረገ ነው።የመጀመሪያዎቹ ከገቢያቸው ከአስር ከመቶ በላይ ከውጪ በጀት የሚያገኙትን ሀገር በቀል የሆኑ ድርጅቶችን ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ የሰብአዊ መብቶችን ከጥቃት የመከላከል ግድታ ያለባቸው የውጪ ድርጅቶች ላይ ያነጣጠረ ነው ብለዋል።

(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

# ርእሰ አንቀጽ

## የጋዜጠኛው ማስታወሻ

የቀድሞው የ"ቡርቃ ዝምታ" ደራሲና፣ የወያኔ "የፕሬስ መምሪያ" ሃላፊ የነበረው ተስፋዬ ገብረአብ የወያኔን ስርአት አስከፊነት ይፋ የሚያደርግ "የጋዜጠኛው ማስታወሻ" የሚል መፅሃፍ በዚህ ሳምንት ለንባብ አብቅቷል ። የ23 አመት ጎልማሳ እያለ በራሱ አነጋገር "የማይመጥነኝን" ያለውን የፕሬስ ዲሬክተርነት ሹመት ከጠቅላይ ሚኒስትር ታምራት ላይኔ የተቀበለው ወጣት፣ በጂፕ ላይ መንጠልጠል የህይወታቸው የመጨረሻ ደስታ አድርገው የሚያዩ ጨቅላዎች፣ ለመለስ ባላቸው ታማኝነት ብቻ እየተመጠኑ በስልጣን ላይ መጎለታቸው፣ ሃገራችንን እየገደላት ነው ሲል በምሬት በመፅሃፉ ውስጥ አትቷል ። ስርአቱ የተቀበላቸውን አለም አቀፋዊ የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎችን በመጣስ ፣ ወፌ ኢላላ ግርፋቶችን እንደሚጠቀምና በተለይ በኦሮሞዎች ላይ ስርአቱ የሚያካሂደውን ብካይ የዐይን ምስክርነቱን ሰጥቷል ።

ስርአቱ የወያኔን የበላይነት ለማስጠበቅ እንዴት አድርጎ ሎሌዎቹን እንደሚጠቀምባቸው "መዝሙረ ዋልዋ" በተሰኘው ምእራፍ በስፋት አትቷል ። "የብአዴን አማራዎች፣ 'ህወሃትን እንደ ራስህ አድርገህ ውደድ' የሚለውን መዝሙረ ዋልዋ ይዘምሩ ዘንድ በትምክህተኝነት መገምገሚያ ይቀጠቀጣሉ ። የ"መስዋእትነት ፍራቻ" የሚለው መገምገሚያ የአማራውን ትምክህት ሊሰብር ይችላል ተብሎ የተዘጋጀ የማሸማመቀቂያ ስልት ሲሆን፣ ሙስና ደግሞ ከስራቸው እንደሚባረሩ የምታስጠነቅቅ ማስፈራሪያ ናት ። በረከተ-ዋልዋና ደቀመዛሙርቱ አባሎቻቸውን በዚህ ዘዴ ገርተው እንደ ቢሾፍቱ ፈረሶች ይጋልቧቸዋል ። ሚዛናዊ የልማት ጥያቄዎችን እንዳያነሱ በተለያዩ የማሸማመቂያ ዘዴዎች ያኮላሹዋቸዋል" ሲልም የተሳተፈባቸው የወያኔ የግምገማ መድረኮችን ይዘት ያጋልጣል ።

የአማራው ህዝብ ለወያኔ ሎሌዎች ያለውን ጥላቻ እንዴት እንደሚገልፅ ሲያስረዳም፣ የጎንደርን አርሶ አደሮች ግጥሞች በመዋስ እንዲህ ብሎታል፣

ጎንደር ሃገር ጠፍቶ - ሲፈለግ ሌሊት፣
ቀን ካዲሱ ጋራ - ሲሄድ አየሁት፣
* * *
መቀሌ ያካፋል - ባድዋ ፀሀይ፣
በጎንደር ጨልሞ - መቅረቱ ነው ወይ፣
* * *
ከሁመራ ገብተን - ከመሃሉ ላይ፣
አዲስ ሰው አገኘን - መሬት መሬት ባይ፣
* * *
ጥቂቶች ቆራጦች - በጣም በርትተዋል፣
ያልተንበረከኩት - ጎንደር ላይ ነግሰዋል፣
አልበቀለም እንጂ - ብዙ ዘር ዘርተዋል፤
* * *

ይህን መሰል የህዝብ ኡኡታዎች በመፅሃፉ ውስጥ በብዛት ተካተዋል ። ደራሲው የመጨረሻውን ቅኔ ሲፈታው፣ "አርሶ አደሩ 'ዘር የሚበሉ' አድርጎ ቆጥሮአቸዋል ። ገበሬ ዘር አይበላም ። ዘሩን ከመብላቱ በፊት መሞትን ይመርጣል ። ለዘር ልዩ ክብር አለው ። ህይወት እንዲቀጥል የዘር እህል ይቀመጣል ። ...ምርጫ 97 ስላልበቀለው ዘር የሚያስገነዝብ አስረጅ ነው ። በረከት ስምኦን ከጎንደር እስከ ቡግና፣ ዘሩን ዘርቶ መከነ ። ህላዌና ተፈራ በአዲስ አበባ የዘሩት ዘር ጫጬ ። ...የህዝቡን ቅኔ አዳምጠው፣ ሰምና ወርቁን መመርመር ይገባቸው ነበር ። ሆኖም የታሪክ ተወቃሽ መሆንን መርጠዋል ። መንገዱን ጨርቅ ያድርግላቸው" ብሎታል ።

ተስፋዬ ገብረአብ መፅሃፉን ሲያገባድድ "ማንነትን መከልከል አመፅን ይወልዳል ። የሃያ አመት ልጅ ሳለሁ የዘመነ ደርግ ባለስልጣን ጋዜጠኛ እንዳልሆን ሲከለክለኝ ትልቅ ነገር ያጣሁ መስሎኝ ለአመፅ ተነሳሳሁ ። በአርባ አመቴ ወያኔ ማንነቴን ሊነጥቀኝ ፈለገ። ወዴት እንደምጓዝ በትክክል አውቃለሁ ። እንዴት እንደምታገልም እገነዘባለሁ ። መብትን ለማስከበር በግልና በድርጅት የሚደረጉ ትግሎች ሳይሳኩ አይቀሩም ። ...በቀጣዩ ዘመን ለራሴ ህልውና ስል እታገላለሁ ። የተነጠቅሁዋቸውን መብቶቼን ለማስመለስ ከመፍጨርጨር ባሻገር ከቶ ምንስ አማራጭ አለኝ?" ይለናል ።

ተስፋዬ ከደርግ የሰራዊት ካድሬነት ጀምሮ፣ የወያኔ ምርኮኛና ታጋይ ሆኖ፣ ከአቅሙ በላይ የሆነ ስልጣን ተሰጥቶት ብዙ ከተንገላታና ካንገላታ በሁዋላ፣ ከህሊናው ጋር ታግሎ "መብቱን ለማስመለስ ሊፍጨረጨር" ወስኗል ። "በታሪክ የተሳሳተ ጎራ የወገኑት የወያኔ አባላት" የተስፋዬ ገብረአብን መሰል ቁርጠኛ ውሳኔ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል ። ከህዝብ ለመወገን ግን፣ እንደ ተስፋዬ መሰደድ አይኖርባቸውም ። የስርአቱን አድልኦና ዘረኝነት በማጋለጥ፣ የህዝባቸውን መብት በመከላከል ፣ ሃገርና ህዝብን የሚጎዱ የመንግስት ምስጢሮችን በማውጣት፣ በህቡዕ ከታጋይ ድርጅቶችና አባላት ጋር በመተባበር፣ ብሎም የማይቀረው የመጨረሻው ግብግብ ሲመጣ "ነፃነት ወይም ሞት" ፈክረው በመነሳት፣ የበደሉትን ሃገርና ህዝብ መታደግ ይቻላቸዋል ። የግንቦት ሰባት ንቅናቄ የተስፋዬ ገብረአብን አይነት የግል ቁርጠኛ ውሳኔ ያደንቃል ። ስለወያኔ ውስጣዊ አሰራር፣ ጭካኔና፣ የመንፈስ ድቀት መረዳት ለሚፈልግ ሁሉ፣ "የጋዜጠኛው ማስታወሻ" በቀላሉ የማይገኝ መስኮት ነው ።

## ታላቅ ህዝባዊ .... (ከገጽ 1 የዞረ)

በአገሪቱ ሰዓት አቆጣጠር ከቀኑ 9 ሰዓት ጀምሮ በተደረገው በዚህ ስብሰባ ላይ ተገኝተው ለተሰብሳቢው የግንቦት 7ን የፖለቲካ አላማና ሁለገብ የትግል ስትራተጂ በሰፊው ያብራሩት የንቅናቄው ከፍተኛ አመራር አባል ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ሲሆኑ ከተሰብሳቢው ለተነሱ ጥያቄዎች ተገቢዉን ምላሽ በመስጠታቸው በስብሰባው ላይ የተሳተፉ ሁሉ ንቅናቄውን በገንዘብ በዕውቀትና በጉልበት ለመርዳት ቃል ገብተዋል። በዚሁ መሰረት ከውይይቱ በኋላ በተደረገው የገንዘብ ማሰባሰብ ዘመቻ በዕለቱ ያልተጠበቀ መዋጮ ተደርጎ ከፍተኛ ገንዘብ ለማሰባሰብ የተቻለ ሲሆን ቁጥራቸው ቀላል ያልሆኑ ግለሰቦች በአባልነት ንቅናቄውን ለመቀላቀል ባደረጉት ውሳኔ አባል ለመሆን የሚያስችላቸውን አስፈላጊውን ፍርማሊቲ ሊያሟሉ የሚችሉበት ሁኔታ ተመቻችቶላቸዋል ። ከዚህም በተጨማሪ በርካታ ሰዎች የግንቦት 7 ንቅናቄ እያካሄደ ያለውን "እኔ ለወገኔ የአርበኝነት ጥሪ" ካርድ በመግዛት የንቅናቄውን ሁለገብ ትግል ለማጠናከር ያላቸውን ቁርጠኝነት ገልጸዋል ።

(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ወያኔ የለኮሰው ... (ከገጽ 1 የዞረ)

ይህ በዚህ እንዳለ ከማንም ሊሰውር በማይችል መንገድ ወያኔ እያቀጣጠለ ያለውን የሀይማኖት ግጭት፤ የእስልምና ጉዳዮች ምክትል ሊቀመንበር ሼህ ኤሊያስ ሬድዋን በተቃዋሚዎች ማላከካቸው የአብዬን ወደ እምዬ የሚለውን ቢሂል እንዳስታወሳቸው ታዛባቢዎች ለግንቦት 7የአዲስ አበባ ዘጋቢ ተናግረዋል።

የሙሲሊሙ ማህበረሰብ በአፍቃሬ ወያኔነታቸው የሚያውቃቸው በንግግራቸው እና ኑሮአቸው ከመንፈሳዊ አባትነት ይልቅ ወደ ካድሬነቱ የሚያመዝኑት ሼህ ኤሊያስ" " .. ከ1997 ዓ.ም. ምርጫ በኋላ አንዳንድ ደስ የማያሰኙ ምልክቶች ይታዩ እንደነበር፣ ምልክቶቹም ከሐይማኖት መሪዎች የመነጩ ሳይሆኑ እምነትን ተገን በማድረግ ሰላምን አደፍርሶ ሕገመንግሥቱን በኀይል ለመገርሰስ የሚደረገው የተቃዋሚዎች እንቅስቃሴ ነው" "ብልው ሲናገሩ መደመጣቸው ያሳዘናቸው የሙሲሊም እምነት ተከታዮች የሰውዬው ንግግር ከመንፈሳዊ አባትነት ይልቅ ወያኔያዊ ተል ዕኮ እንዳላቸው በግልጽ የሚያሳይነው ብሎአል።

በታላቁ አንዋር መስጊድ ወያኔ በ1987 ኢ.ም አረመኔያዊ ጭፍጨፋ ካካሄደ እና እነ መሀመድ አመዴን አስሮ የእስልምና ምክር ቤት ሊቀመንበር እና የታላቁ አነዋር መስጊድ ኢማም ሼሀ ኑርን መንፈሳዊ አገልግሎታቸውን እንዲያቆሙ ጫና በሚያድርግበት ጊዜ ሼህ ኤሊያስ አላህን ለማገልገል ባለቸው ፍላጎት እና በመንፈሳዊ እውቀታቸው ሳይሆን በካድሬነታቸው ቦታው እንደተሰጣቸው ለዘጋቢያችን የተናገሩት ለአንዋር መስጊድ ቅርበት ያላቸው ሙሲሊም፤ (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ለካናዳ መንግስት ... (ከገጽ 1 የዞረ)

የፓርላማ ተመራጪ ፤ ከምርጫ 97 በኋላ የሰብአዊ መብት ሁኔታ በእጅጉ አስከፊ ደረጃ ላይ ደርሶ ከ200 መቶ በላይ ሰዎች በግፍ መገደላቸውን፤የተቀዋሚ መሪዎች ፤የሰብአዊ መብት ተሚጋቾች እና ጋዜጠኞች በወህኒ ለሁለት አመት ያክል መማቀቃቸውን እና በቅርብ የወ/ት·ብርቱካን ሚደቅሳ እንደገና በእብሪት መታሰሯን ለካናዳን ጠቅላይ ሚኒስትር ካስታወሱ በኋላ የካናዳ መንግሰት በአስከፊ ሁኔታ ሰብአዊ መብትን የሚረግጥ እና የፕሬስ ነጻነት የሚጋፋን ጨቋኝ አገዛዝን የመጋፈጥ ሀላፊነት አለበት በማለት ማሳሰባቸውንም ለማወቅ ተችልችቿል። በተጨማሪም ካናዳ በአለም በሰብአዊ መብት አያያዝ ቀዳሚ እንደመሆኗ ጠቅሰው ጨቋኙን የመለስ አገዛዝን ማውገዝ እና አለማ አቀፍ ማህበረሰብ ለተግባር እነዲነሳሳ ጫና ማድረግ አለባት ሲሉ መንግሥታቸውን በጽኑ አሳስበዋል ።

(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)



የፖስታሳጥን ቁጥር ፡- POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

# ሃይለ ሀሳብ

## ምን ላይ ስንደርስ ነው በቃን የምንለው?

ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ

ባለፈው ማክሰኞ የኦባማን ቃለመሀላ በአንድ ላይ ሆነን በቴሌቪዥን ስንከታተል ቆይተን የነበረች አንደ የስራ ባልደረባዬ በዛሬው እለት ወደዚህ ወደ ዳላስ እንደምመጣ ስትሰማ በመገረም ቢሮዬ ደውላ ምን ልታደርግ ነው እዚያ የምትሄደው? እዚያ ማን እንደሚኖር ታውቃለህ? ቡሽ እኮ እዚያ ሊኖር ሄዶአል? አይቀፍህም ዳላስ መሄድ? ደሞስ ልክ እሱ በሄደ ጊዜ የምትሄደው፤ ከሱ ጋር ጉዳይ ኖሮህ ነው እንዴ? ብላ አፋጣ ጠየቀችኝ፡፡ ለሌላ ጉዳይ እንደሆነ የምሄደው እየሳቅሁ ከነገርኩዋት በሁዋላ ትንሽ ነገሩን ሳስበው የገረመኝ ለኔ ዳላስ ማለት ዳላስ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ማለት እንጂ ከዚያ ውጭ ምንም ትርጉም እንደሌለው፤ የቡሽ ዳላስ ለመኖር መወሰን ትንሽም እንኩዋን ጭንቅላቴ ውስጥ እንዳልደወለ፤ ለአሜሪካኑዋ ግን ቦታውን የምታያይዘው በአገሩዋ ላይ ቡሽ ካደረሰው በደል ጋር አዛምዳ መሆኑ፤ አንድ ቦታ እየኖርን፤ ተመሳሳይ ስራ እየሰራን ሀሳባችንና ስሜታችን ምን ያህል የተለያየ እንደሆነ ነበር የታየኝ፡፡ የዚያኑ ያክል ግን እኛ ኢትዮጵያውያን የትም ኖርን የትም የምናስበው፤ የምናሰላስለው፤ ከቁምነገር የምንወስደው፤ የምንተክዝበት፤ የምናላዝንበት፤ ሌት ተቀን የምንቆጭበት፤ ውርደቱ ቆዳችንን ዘልቆ የሚሰማን፤ ከስራ ስንመለስ ‹ምን ወሬ አለ› ብለን የምንደበርበት ይህንንው የአገራችንን ጉዳይ መሆኑንና የውጭ አገር ኑሮውም ውስጡ ገብተን እንደነሱ ሙሉ ልባችንን ሰጥተን፤ አገሩን አገራችን ብለን ለመኖር ምን ያህል እንደሚቸግረንም ነበር እያሳየኝ የነበረው፡፡ የመጀመሪያ ትውልድ የስደተኛ ኑሮ፡፡

ይታያችሁ፡ እነኝህን ነገሮች የማስበው በአሜሪካ የቅርብ ጊዜ ታሪክ የተለየና ታሪካዊ የሆነ ክስተት በሚታይበት፡ ሁለት የተቆራኙ ከበደል ጋር በሚደረግ ትግል አንድም ሀዘንን ሌላም ድልንና ደስታን የሚያበስሩ ቀኖች በተጋጠሙበት፤ እኛ ኢትዮጵያውያን ካለንበት ሁኔታ ጋር በመንፈስ የተዛመዱ ሁለት ክስተቶችን ፊት ለፊት እያየን በምንገረምበት፤ በማርቲን ሉተር ኪንግ የልደት በአል ቀንና የባራክ ኦባማን የመጀመሪያው ጥቁር አሜሪካዊ ፕሬዜዳንት ሆኖ ቃለመሀላ የፈፀመበትን ቀን ሚሊዩኖች በደስታ ሲቃ እየጮሁ በሚያከብሩበት ጊዜ ነው፡፡

የዴሞክራሲን ታምራዊ ጨዋነት፤ ኑሮ እየከበዳቸው የአገራቸው ኢኮኖሚያዊና አለም አቀፋዊ አካሄድ ቀድሞ በመረጡት መንግስት ድንቁርናና ግብዝነት ምክንያት ፈተና ውስጥ እንደተዘፈቀ እያወቁ እንኩዋን በፖለቲካ ስርአታቸው ክፍትነትና እራሱን የማከም ችሎታ በመተማመን፤ ክፉ ታሪካቸውን ‹ሆኖ አያውቅም› ከሚል አውቆ መርሳት ወይንም የዚህ ታሪካቸው እስረኛ ከመሆን ይልቅ ይህ ታሪክ ነስቶአቸው የነበረውን በዘረኛነት አድሎ ምክንያት አጥተውት የነበሩትን የብዙ ዜጎቻቸውን ክህሎት በፀፀት እንደገና አቅፈው፤ በከፍተኛ ተስፋና ወንድማማችነት ጥቁሩ ከነጩ፤ ወንዱ ከሴቱ፤ ክርስቲያኑ ከሙስሊሙና ከይሁዲው ጋር እጅ ለእጅ ተያይዞ በሙሉ ተስፋ የወደፊት ሕይወታቸውን ሲቀበሉ ስናይ፤ እርግጠኛ ነኝ ብዙ ኢትዮጵያውያን በአእምሮአቸው ይዞር የነበረው ስሜት ‹መቼ ነው እኛስ እንደነሱ የምንሆነው>? መቼ ነው የኛስ አበሳ የሚያልቀውና እጅ ለእጅ ተያይዘን ለአገራችን ችግሮች መፍትሄ ሊሰጡን የሚችሉ መሪዎቻችንን የምንመርጠው? መቼነው አገራችንን እዚህ ደረጃ ሊያደርሱ የሚችሉ አላሚዎችን በችሎታቸውና በምግባራቸው እንዲሁም ለአገራችን ባላቸው ራዕይ እንጂ የዘውግ ወይንም የሀይማኖት ጀርባቸውን እያየን መመዘን የምናቆመው? መቼ ነው ከአፍንጫ በማያልፍ ጠባብና ጊዜያዊ የግል ጥቅም ላይ በማተኮር ከምናጠፋው ማለቂያ የሌለው፤ በክፋት የተሞላ፤ ለማናችንም ምንም ትርፍ የማያመጣ አስቀያሚ ንትርክ ይልቅ ዘላቂ በሆኑ ለትውልድ በሚተርፉ መሰረታዊ የጋራ ጥቅሞች ላይ አትኩሮታችን የሚያርፈውና በነኛ ጉዳዬች ላይ የምንረባረበው? መቼ ነው እንደ አገርና እንደ ሕዝብ እንዴትና ወዴት ነው የምንሄደው የሚሉት ማቆሚያ የሌላቸው ክርክሮች አብቅተው መሄድ ወደምንፈልግበት ቦታ የሚወስደንን ስራ ሸሚዛችንን ጠቅልለን መስራት የምንጀምረው? የሚል አወንታዊ የመንፈሳዊ ቅናት ስሜት ይመስለኛል፡፡

ይህ እንግዲህ ባህሪያቸው ሆኖ አብሮ ለማደግ የራሳቸውን አስተዋፅኦ ከማድረግ ይልቅ የሌላውን መውደቅ በመሻት ብቻ ሙሉ ጊዜያቸውን የሚያጠፉ፤ በመንፈሳዊ ቅናት ከበጎ ነገር ትምህርትን ከመቅሰምና የዚህ በጎ ነገር ተቁዋዳሽ ከመሆን ይልቅ የሌላው በጎ መሆን በውስጣቸው እንደ ካንሰር የተንሰራፋውን ክፉ ምቀኝነት የሚያላውስባቸውን ጥቂት ያገራችንን (ወይንም የሌላ ሀገር) ህመምተኞች አይጨምርም፡፡

በዚያው ልክ የገረመኝ ግን የአብዛኛው ኢትዮጵያዊ ሰሜት ይህ ከሆነ ታዲያ ይህን ያክል የምንጨነቅለትን አገር፤ ውርደቱ ይህን ያክል እንቅልፍ የሚነሳንን አገር ተባብረን ለሁላችንም የሚሆን፤ ሁላችንንም በእኩልነት የሚያይ፤ በዜግነታችን የምንከበርበትና የምንኮራበት አገር ማድረግ እንዴት ተሳነን? እንዴት ነው በአንድ አይነት የውርደት መቀመቅ ውስጥ የምንኖር ሰዎች ተባብረን ከዚህ ውርደት ለአንዴና ለሁሌም ለመገላገል የተሳነን? እንዴት ነው ይህ ያለማቁዋረጥ የምናወራለት “የሀገር ፍቅር” የአገሩን ህዝብ አፋቅሮ ቢያንስ በጋራ ወደምንስማማበት ስርአት ሊወስደን ያልቻለው? ወይንስ ለኛ ለኢትዮጵያውያን ከሕዝቡ በፍፁም የተነጠለና ለአፈሩና ለውሀው ብቻ የሚያገለግል የተለየ የአገር ፍቅር አለን? የሚለው የእኛነታችን ውጥንቅጥ ነበር የሚያስደምመኝ፡፡

እኔም እነኝህን ቀኖች እያሰብኩና በእለቱ ተመራጩ ፕሬዜዳንት የተናገረው ቃል በጆሮዬ እያቃጨለ ነበር እነኛህን ታዲያ እኛን ምን ነካን? የሚለውን ከላይ ያነሳሁዋቸውን የተያያዙ ጥያቄዎች እንዳነሳ ያስገደደኝ፡፡ የዛሬን አጭር አስተያየት የማቀርበውም እነኝህ የሰሞኑ የአሜሪካ ክስተቶች በኛነታችን ላይ የጫሩዋቸውን ጥያቄዎች ለመነካካትና አወንታዊ ውይይት ለመጎንተል ነው፡፡ ይህ ፍተሻ እንደዚህ በአጭር ንግግር የሚጠቃለል እንዳልሆነ መቼም ሁላችንም እንረዳለን፡፡ ብዙ በጣም ብዙ የማህበረሰባችንን ምንነቶች የሚነኩ ስነልቦናዊ፤ ማህበራዊ፤ ታሪካዊ፤ ሀይማኖታዊ ጉዳዬችን ሁሉ የሚዳስሱ ሰፋፊ ጥናቶችን የሚጠይቁ ከኔም እውቀት በላይ የሆኑ ቁምነገሮች የተካተቱበት ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ዛሬ የተሰበሰብንበት ደግሞ ‹ምሁራዊ ሴሚናር› ሳይሆን የፖለቲካ ስብሰባ ነው፡፡ ያውም በአንድ ድርጅት የተጠራ፤ የድርጅቱን አቅዋሞች ለማስተጋባትና ለድርጅቱም እንቅስቃሴ ድጋፍን ለማሰባሰብ የተጠራ፡፡ ስለሆነም የንግግሬን ዋና ትኩረት አጥር ሰርቼ በተለይ ከፖለቲካው አኩዋያ በጣም አጣዳፊ ናቸው በምላቸው አንድ ሁለት ጉዳዮች ላይ አነጣጥሬ ከተሳካልኝ ለምን በአገራችን የሚደረገውን የዴሞክራሲ ትግል ከወሬ አልፋችሁ በተግባር መደገፍ እንዳለባችሁ በተለይም ደግሞ አባል የሆንኩበትን ድርጅት ግንቦት ሰባትን እንድትደግፉና ቢቻል እንድትቀላቀሉ ለማሳመን ነው የምጥረው፡፡

ይህን ውይይት ለማድረግ ጥሩ መነሻ የሚሆነው ከአእምሮአችን በስተጀርባ እውነት መሆናቸውን በምንቀበላቸው ወይንም ጥያቄ ውስጥ በማይገቡ ጉዳዮች ላይ አንተርሼ ብጀምር ነው፡፡ የመጀመሪያው ነጥብ በግንዛቤና በተግባር መሀከል ያለው ግንኙነት ነው፡፡ በእኔ እምነት በተግባር የምንገልፃቸው ስራዎቻችን ሁሌም ባይሆን አብዛኛውን ጊዜ አውቀንና አስልተንም ሆነ እንዲሁ በደመነፍስ ከሰበሰብነው ስለ ጉዳዩ ካለን ግንዛቤ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በአንድ ጉዳይ ላይ የጠራ ግንዛቤ ከሌለን ተግባራዊ እንቅስቃሴያችንም የዚያኑ ያክል መሰረት የያዘ አይሆንም፡፡ የጠራ ግንዛቤ ለመያዝ ደግሞ በጉዳዩ ላይ ጠንቅቆ ማሰብን፤ አስፈላጊ ከሆነ የሚነበቡ ነገሮችን ማገላበጥን ሊጠይቅ ይችላል፡፡ በተግባር የሚገኝም ሆነ በንባብ የሚገኝ እውቀት ደግሞ በስንፍና የሚሆን ነገር አይደለም፡፡ ስራ ይጠይቃል፡፡ የአእምሮ ክፍትነትን ይጠይቃል፡፡ የሌላውን ለማዳመጥና ከዚያም የሚገኝ እውቀት ካለ ለመቅሰም የተከፈተ አእምሮ ከሌለ፤ የያዙትን አቅዋም ብቻ ለማስተጋባት ከሚሻ የውይይትና የጥናት መንፈስ እውቀት ይገኛል ተብሎ አይታሰብም፡፡ እኛ ኢትዮጵያውያን እንደዚህ በአብዛኛው የምንስማማባቸውንና ለሁላችንም እንደሚያስፈልጉ ያመንንባቸውን ቁምነገሮች ተግባራዊ ለማድረግ ለምን ተሳነን የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ስንሞክር ቢያንስ በጉዳዩ ላይ ያለን ግንዛቤ ተቀራራቢ ነው፤ ልዩነቶች ቢኖሩም በደንብ ካሰብንባቸው በተግባር ሊያስተባብሩን የሚከለክሉ አይደሉም፤ የሚል መነሻ እምነት ይዤ ነው ውይይቱን የምቀጥለው፡፡ ይህም ማለት እንደ አገርና እንደ ሕዝብ አብዛኛዎቻችን የምንፈልገውን እናውቃለን ብቻ ሳይሆን የምንፈልገውም ነገር ተቀራራቢ ነው ብዬ አምኜ ነው ቀጣዩን ውይይት የማደርገው፡፡ ይህ ማለት ሁላችንም አንድ አይነት ግንዛቤ አለን ማለት አይደለም፡፡ ፍፁም የተለየ አመለካከትና ግንዛቤ ያላቸው ሰዎች ተግባራዊ ድርጊታቸውም የተለየ ቢሆን ተገቢ ነው፡፡ ድርጊታቸውን ግንዛቤያቸው ይወስነዋልና፡፡ ስለዚህም ለምን በተግባር መስራት ያለብንን መስራት አቃተን የሚለው ውይይት፤ ግንዛቤያችን ተመሳሳይ ሆኖ፤ የምንፈልገው ነገር ተመሳሳይ ሆኖ፤ ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ያቃተበትን ምክንያት ለማወቅ የሚደረግ ሙከራ ነው ማለት ነው ውይይቱ የሚሆነው፡፡

ከዚሁ ጋር የተያያዘና ከላይ ያነሳሁትን መንደርደሪያ ሀሳብ መሬት የሚያስረግጥ ተግባራዊ ምሳሌ ሰጥቼ ወደ ዋናው ርእሴ ልግባ፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ በቂ ዴሞክራሲያዊ ስርአት አለ (ምናልባትም እንከን የለሽ እንኩዋን ባይሆን)፤ ቢያንስ ቀስ እያለ ወደዚያ መስመር የሚሄድ መንግስት አለን ብሎ የሚያምን ሰው፤ ይህንን ስርአት ለመጣል በሚደረግ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ለምን አትሳተፍም ብሎ መጠየቅ ትርጉም የሌለው ነገር ነው፡፡ ምክንያቱም ከመነሻው ይህ ስርአት መለወጥ የለበትም ብሎ ያምናልና! በተመሳሳይ መንገድ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ስርአት ዴሞክራሲያዊ አለመሆኑን አውቆ፤ ይህ መንግስት መውደቅ እንዳለበት አምኖ፤ ግን በዚያ መንግስት ምትክ የሚቀመጠው ዴሞክራሲያዊ ስርአት ሳይሆን በተራው ረግጦ የሚገዛ፤ በሌላ ምክንያት ስልጣን ይገባኛል ብሎ የሚያምን ሀይል ነው ብሎ ከልቡ የሚያምን ሰው ወይንም ሀይል ሊመጣ የሚገባው ለውጥ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ብቻ ነው ብሎ ከሚያምን ሀይል ጋር በጋራ ስለሚደረግ ተግባራዊ ትግል መነታረክ ዝም ብሎ ጉንጭ ማልፋት ነው የሚሆነው፡፡ ቢወራም መሰረታዊ ግንዛቤን ለማስቀየር

የሚደረግ ክርክር ነው በመጀመሪያ መደረግ የሚኖርበት፡፡ ከዚሁ ጋር የተያያዘና ከላይ ያነሳሁትን መንደርደሪያ ሀሳብ መሬት የሚያስረግጥ ተግባራዊ ምሳሌ ሰጥቼ ወደ ዋናው ርእሴ ልግባ፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ በቂ ዴሞክራሲያዊ ስርአት አለ (ምናልባትም እንከን የለሽ እንኩዋን ባይሆን)፤ ቢያንስ ቀስ እያለ ወደዚያ መስመር የሚሄድ መንግስት አለን ብሎ የሚያምን ሰው፤ ይህንን ስርአት ለመጣል በሚደረግ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ለምን አትሳተፍም ብሎ መጠየቅ ትርጉም የሌለው ነገር ነው፡፡ ምክንያቱም ከመነሻው ይህ ስርአት መለወጥ የለበትም ብሎ ያምናልና! በተመሳሳይ መንገድ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ስርአት ዴሞክራሲያዊ አለመሆኑን አውቆ፤ ይህ መንግስት መውደቅ እንዳለበት አምኖ፤ ግን በዚያ መንግስት ምትክ የሚቀመጠው ዴሞክራሲያዊ ስርአት ሳይሆን በተራው ረግጦ የሚገዛ፤ በሌላ ምክንያት ስልጣን ይገባኛል ብሎ የሚያምን ሀይል ነው ብሎ ከልቡ የሚያምን ሰው ወይንም ሀይል ሊመጣ የሚገባው ለውጥ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ብቻ ነው ብሎ ከሚያምን ሀይል ጋር በጋራ ስለሚደረግ ተግባራዊ ትግል መነታረክ ዝም ብሎ ጉንጭ ማልፋት ነው የሚሆነው፡፡ ቢወራም መሰረታዊ ግንዛቤን ለማስቀየር የሚደረግ ክርክር ነው በመጀመሪያ መደረግ የሚኖርበት፡፡ ነገሩን የበለጠ ለማነጣጠር ያክል ይህ መንግስት ኢዴሞክራሲያዊ ነው፤ መውደቅ አለበት፤ ለመጣል የሚቻለው ግን በራሱ ሕግ ማዕቀፍ ውስጥ ሆኖ በሚደረግ (በተለይም ደግሞ በምርጫ ውድድር ነው) ብሎ ከሚያምን ሰው ወይንም ሀይል ጋር ከምርጫ ውጪ በሚደረግ አመፅ ብቻ ነው የሚወድቀው ብሎ የሚያምን ሀይል እኔ በመረጥኩት የትግል ስልት ዙሪያ ለምን በጋራ ተግባራዊ እንቅስቃሴ አናደርግም ብሎ ችክ ማለት፤ እንደዚሁ በግንዛቤና በተግባራዊ እንቅስቃሴ መሀከል ያለውን ዝምድና ካለመረዳት የሚመጣ ነው የሚሆነው፡፡ ይህን ሁሉ ስል አንደኛው መስመር ከሌላው ይሻላል የሚል መስመር በማራመድ አይደለም፡፡ በጥቅሉ ዛሬ በአጭሩ ለመወያየት የመረጥኩት ጉዳይ እንደዚሕ አይነቶቹን ልዩነቶች መሰረት ያደረገ ሳይሆን፤ እነኝህ ልዩነቶች በሌሉበት፤ በችግሩ አይነት፤ በአላማ፤ በግብ፤ ወደግቡ ሊወስድ የሚችለው የትግል መስመር የትኛው ነው በሚለው ስሌት...ወዘተ ሁሉ አንድ አይነት ግንዛቤ ባላቸውም ሀይሎች መሀከል እጅ ለእጅ ተያይዞ ችግሩን ለማስወገድ ከመታገል እንቅፋት የሆነው ምንድን ነው የሚለውን ጥያቄ ነጥሎ ለመመርመር ያክል ነው፡፡

ለግልፅነት እንዲረዳ በዚህ ጉዳይ ላይ የራሴንና የድርጅታችንን አመለካከት ከወዲሁ ግልጽ ላድርግ፡፡ በመለስና በበረከት የሚመራው የወያኔ/ኢሕአዴግ ቡድን በኢትዮጵያ ውስጥ ዴሞክራሲያዊ ስርአት እንዲመሰረት በፍፁም አይፈልጉም፤ ማንኛውንም ጥያቄ የሚመለከቱበት መነፅር ራሳቸውን ከስልጣን ከማቆየት አንፃር ብቻ የሚያሳያቸው ነው፤ በመጠኑም ቢሆን ዴሞክራሲያዊ የሆነን ውድድር በግንቦት 97 ምርጫ የፈቀዱት ስለራሳቸው ተቀባይነትም ሆነ ስለድርጅታቸው ጥንካሬ ካላቸው የተሳሳተ ግምት በመነሳት ማሸነፋቸውን እርግጠኛ በመሆናቸው እንጂ ቅንጣት የምታክል የዴሞክራሲ ወገንተኛነት ስለነበራቸው አይደለም፤ ከምርጫው በሁዋላ የወሰዱት እርምጃና አሁንም እየወሰዱ ባሉት እርምጃ ይህንን በማያወላዳ መልክ ለወዳጅም ለጠላትም ግልፅ አድርገውታል፡፡ ስለዚህ በዚህ ጉዳይ ላይ ምንም ሊያከራክር የሚገባው ነገር የለም ብለን እናምናለን፡፡ ይህን የምንለው ደግሞ እንደዚሁ በሩቁ በስማ በለው ከሰማነው ወይንም ቤተ መጻህፍት ተቀምጠን የተፃፉ ነገሮችን በማየት ሳይሆን በጣም በቅርብ ሆነን አይተናቸው፤ ከሚገባቸው በላይ ትክክለኛውን መስመር ሊከተሉ ይችላሉ የሚል ቅን ልቦና ሰጥተን ተከታትለናቸው፤ ወደ ቀናው መስመር እንዲሄዱ መክረን፤ ተስፋችንን አሙዋጠው ከጨረሱት በሁዋላ ነው፡፡ እነኝህ ሰዎች ኢዴሞክራሲያዊ ብቻ ሳይሆኑ፤ ለአንዲት ተጨማሪ ቀን እንኩዋን በስልጣን ለመቆየት እስካስቻላቸው ድረስ የማያደርጉት ምንም አይነት እኩይ ተግባር እንደሌለ፤ ምንም የሞራል ልጉዋም እንደሌላቸው፤ ከራሳቸው ስልጣን አስበልጠው የሚያዩትና ስልጣናቸውን በፈቃዳቸው ሊያስለቅቃቸው የሚችል ምንም የአገር፤ የዘውግ/የብሄር፤ የሕዝብ፤ የእምነት ወይንም ሌላ ሰማያዊ ጥቅም እንደሌለ በተግባር አረጋግጠን ነው፡፡ በዚህም ምክንያት እያንዳንዱ እነሱ በስልጣን የሚቆዩበት ቀን ለአገራችን፤ ለሕዝቡዋ፤ ለመጪው ትውልድ በጣም አደገኛ የሆነ ሁኔታን የሚፈጥርና መመለሻ የሌለው ማጥ ውስጥ የሚከተን፤ እዚያ ከመድረሳችን በፊት በአስቸኩዋይ ይህን መንግስት ማንኛውንም መንገድ ተጠቅመን ማስወገድ አለብን የሚል ጥልቅ እምነትና በተቻለ መጠን በመረጃ ላይ የተመሰረተ ትንታኔ ሰጥተን የደረስንበት መደምደሚያ ነው፡፡

ይህም ስለሆነ ከስልጣናቸው ተገደው እንጂ ወደው አይለቁም ብለን ደምድመናል፡፡ ከዚያም አልፈን ይህንን የማስገደድ ስራ ልንሰራ የምንችለው እኛው እራሳችን ተባብረንና ቆርጠን በምናደርገው ትግል እንጂ፤ ማንም የውጭ ሀይል አስር ጊዜ በአላማ ደረጃ ከኛ ጋር ቢስማማ፤ ሺህ ጊዜ በሕዝቡ ላይ በሚደርሰው አበሳ ቁጣውን ቢገልፅ፤ ወያኔ/ኢሕአዴግን ምናልባት ያዳክምልን እንደሆነ እንጂ (ያም በጣም ምናልባት ነው) በፍፁም አይጥልልንም፡፡ እነመለስ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚበላው አጥቶ ቢረግፍ፤ የሚለብሰው አጥቶ እራቁቱን ቢሄድ፤ በውጭ ተፅእኖ እንደ ዚምባብዌ ኢኮኖሚው ተንኮታኩቶ ቢወድቅ፤ ማህበረሰቡ እርስ በእርሱ ቢባላ፤ እንደ ሙጋቤ የመጨረሻ ትንፋሻቸውን እስከሚተነፍሱ ድረስ በስልጣን ለመቆየት ይሞክራሉ እንጂ የውጭ አገሮች እርዳታ ይቆምብናል ብለው ከስልጣን መውረድ አይደለም፤ ስልጣናቸውን ትንሽ እንኩዋን የሚሸራርፍ ድርድር በፈቃዳቸው (ከልባቸው) ይገባሉ ብለን አናምንም፤ አማራጩ በሀይልም ቢሆን መወገድ መሆኑን ያለምንም ማወላዳት ካላመኑ በቀር፡፡ እዚያ ቦታ ላይ ደግሞ የምናደርሳቸው እኛው በትግላችን ብቻ ነው፡፡

በመጨረሻም እኛ እንደ ግንቦት ሰባት ከአሁን በሁዋላ በኢትዮጵያ መመስረት ያለበት የፖለቲካ ስርአት እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ስርአት፤ ከሕዝብ ይሁንታ ውጪ ማንም ሀይል በአገራችን በማንኛውም እርከን የፖለቲካ ስልጣን ላይ የማይወጣበት፤ የሁሉም ዜጎች የግለሰብና የወል መብቶች ሙሉ በሙሉ የተከበሩበት፤ መንግስት ሕዝብን የሚፈራበትና የሚያከብርበት፤ እውነተኛ ነፃ ተቋማት ያሉበት፤ ለዘመናት የቆዩ በውስጣችን ያሉ ቁስሎች የሚሽሩበት፤ ከሰሞኑ በዚሁ በአሜሪካ እንዳየነው እኛም ከታሪካችን እውነተኛውን ትምህርት የምንቀስምበት፤ እውነትና ሀቅን የመሰሉ መሰረታዊ የሞራል እሴቶቻችን በፖለቲከኞቻችን፤ በመንግስት ባለሙዋሎች፤ በሀይማኖት መሪዎቻችንና በአጠቃላይ በሕዝቡ ውስጥ እንደገና የሚያብቡበት፤ እንደዜጎች እርስ በእርሳችን የአንድ እጣ ተጋሪ መሆናችንን አውቀን በዜግነት እኩልነት ላይ የተመሰረተ የወዳጅነት ትስስር የምንመሰርትበት ጤናማ ስርአት ሊሆን ይገባል ብለን በፅኑ እናምናለን፤ የምንታገለውም ለዚሁ ነው፡፡

እንግዲህ የኛን እምነት በግልፅ ካስቀመጥንና በእምነትና በግንዛቤ ደረጃ ብዙዎቻችን እነኝህን እምነቶች እንጋራለን ብለን ወስደን ነው ታዲያ ተባብረንና ተደጋግፈን ይህንን አስከፊ ስርአት ለመጣል ለምን ቸገረን የሚለውን ጥያቄ ለማየት የምንሞክረው፡፡ ከኛ የተለየ አመለካከት ያላቸው ወገኖቻችን እንዳሉ እናውቃለን፡፡ ይህን ልዩነታቸውንም እናከብራለን፡፡ ከነሱ ጋር ያሉንን ልዩነቶች በህዝብ ፊት ቀርበው በህዝብ ምርጫ ለመዳኘት እስከወሰንንና ይህንንም ከልባችን እስከተቀበልን ድረስ ሁላችንም መስመራችንን ይዘን መሄዳችን ችግር የለውም፡፡ ጤናማም ነው፡፡ አሁን የምናደርገው ውይይት ግን በነኝህ እምነቶች ላይ ስምምነት ባላቸው ወገኖችና ሰዎች መሀከል የተቀናበረ የጋራ ግፊት ለማድረግ ለምን ይሳነናል የሚለውን ጥያቄ በአጭሩ ለመዳሰስ ነው፡፡

( በሚቅጥለው እትማችን ይቀጥላል)

## ወያኔ የለኮሰው.... (ከገጽ 2 የዞረ)

ሼህ ኤሊያስ ቅንጣት ታክል መንፈሳዊነት ቢኖረው ሌላውን ትተን በቅርቡ እንኳን መስጊዳችን አካባቢ በወንድሞቻችን ላይ ስለደረሰው ግፍና ድብደባ ሊያወሩ ይገባ ነበር ብለዋል።እኙሁ አማኝ ቀጥለውም ሙስሊሙ እና ክርስቲአኑን ሊያጣል የሚችል ምንም ምክንያት የለም ብቻ ሳይሆን የሁለቱ እምነት ተከታዮች በሀዘን በደስታ የማይነጣጠሉ እና ለረጅም ዘመናት በደም እና በባህል በተገመደ ወፍራም ገመድ መተሳሰራቸውን አስታውሰዋል። በመቀጠልም በቅርቡ በአሩሲ የእስላም ቀብር ሩቅ ቦታ ስለነበር ለቀብር ረጅም መንገድ የሚሄዱት ክርስቲያኖች ሁኔታ ያሳሰባቸው ሙስሊሞች በአቅሪቢያቸው የሚገኝን የግል መሬታቸውን ለቀብር መስጠታቸውን ስንሰማ፤በወሎ አም ዲሊላሂ ታቦታችን በሰላም ገባ እየተባለ፤እዚህ መርካቶ ሁነኛው ተራ ለዘመናት አክሊል፤ የቤተክርስትያን አልባሳትን፡የንዋየ ቅድሳትን መሸፈኛ ሙስሊሙ እየሰፋ ለክርስቲያን ወንድሙ በሚሸጥበት ሀገር፤ክርስቲያኑም ሆነ ሙስሊሙ ሰርግ ሲደግስ በእምነቱ መሰረት ምግብ ለብቻው አዘጋጅቶ የሚገባበዝ ወንድማማች እና በፍቅር የኖረን ህዝብ ወያኔ ካልቀሰቀሰው በቀር እንደምን ሊጋጭ ይችላል ሲሉ ለዘጋቢያችን ጥያቄ አንስተዋል።

ወያኔ በምርጫ 97ዋዜማ መሸነፉን እውን እንደሚሆን ሲያውቅ ህዝቡ ለመከፋፈል ከተጠቀመባቸው ጉዳዮች አንዱ ሀይማኖት እንደነበር እና ቅንጅት ሙስሊሞችን ለመጨቆን እንደመጣ ሀይል አድርጎ በቀቢጸ ተስፋ ለመሳል ቢሞክርም እንዳልተሳካለት የሚታወስ ነው። ከምርጫውም በኋላ እነ ተፈራ ዋልዋን በመሰሉ ህሊና አልቦ ጀሌዎቹ እገሌ ቤተክርስትያን የነፍጠኞች ዋሻ ነች የሚል ጻያፍ ማስነገሩ እና ጽሁፍች ማሳታሙ የሚታወስ ነው።የዝግጅት ክፍላችን እነደ ቋያ እሳት እየተቀጣጠለ ሊሄድ ከሚችል እሳት እራሱን ጠብቆ ሀገሩን እና ህልውናውን ለማጥፋት ቆርጦ በተነሳው ወያኔ ላይ ብቻ ማነጣጠር እንዳለበት በድጋሚ ያሳስባል።

## ለካናዳ መንግስት ... (ከገጽ 2 የዞረ)

ባለፈው ሳምንት አራት የአሜሪካ ሴኔት ላቃነመናብርት የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በተቃዋሚ ፓርቲዎች ላይ እያደረሰ ያለውን እስርና እንግልት በአስቸኳይ እንዲያቆምና የአንድነት ለፍትህና ለድሞክራሲ ፓርቲ ፕሬዝደንት ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳንና ላልችንም የፖለቲካ እስረኞች በአፋጣኝ እንዱፈታ ፤በማሳሰብ ይህ የማይሆን ከሆነ ከአሜሪካ ጋር ያለው ግኑኝነት ክፉኛ ላጎዳ እንደሚችል ማስጠንቀቃቸው ይታወሳል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በንጹሀን ኢትዮድያውን ላይ ወያኔ የሚፈጽመውን ዘግናኛ ግፍ እና ግዙፍ የሰብአዊ መብት ጥሰት እየተከታተለ ሲያጋልጥ የነበረው አንጋፋው የሰብአዊ መብት ድርጅት ኢሰመጉ ወደ መዘጋቱ እያመራ እንደሆነ በድርጅቱ ውስት የሚሰሩ አንድ ስማቸው እንዳይገለጽ ያፈለጉ የሰብአዊ መብት ተሟጋች ለግንቦት 7 የአዲስ አበባ ዘጋቢ ገለጹ።ኢሰመጉ ሙለ ለሙለ በጀቱን ከሀገር ውጪ ካሉ ለጋሾች እንደሚያገኝ የተናገሩት የሰብአዊ መብት ተሟጓቹ ድርጅቱ ከዚህ በኋላ በምንም ተአምር ስራውን ለመስራት እንደማይችል እና ከአሁኑ አሜሪካ ለሚገኘው የድጋፍ ድርጅት ብዙ ሀላፊነቱን ለማስተላለፍ መገደዱን ጠቁመዋል። ኢትዮድያውያን ከመቼውም ጊዜ በከፋ ሁኔታ የሰብአዊ እና የዜግነት መብታቸው እየተረገጠ እና መረን ለለቀቀ ጭቆና እየተጋለጡ ባለበት ወቅት ጸረ የሰብአዊ መብት ድርጅቶች ህግ መጽደቁ አንድም ወያኔ የሚሰራውን ግፍ ህጋዊ ለማድረግ መቁረጡን ያሳያል አንድም በኢትዮድያችን ነጻ ማህበረሰብ ለመፍጠር ቀርቶ ለማሰብም እንደማይቻል መልእክት እየተላለፈልን ነው ብለዋል የሰብአዊ መብት ተሚጋቹ። በወያኔ ፓርላማ ጸደቀ የተባለው አፋኝ ህግ ከዘረዘራቸው አንቀጽ ውስጥ አንዱን ተላልፎ የሚገኝ የሰብአዊ ተማጋች ድርጅትም ሆነ ግለሰብ በቀሪ ህይወቱ በጠቅላላ በሰብአዊ መብት ፤በዳሞክራሲ እና ግጭት አፈታት ላይ እንዳይሰራ እቀባ እንደሚያደርግበት የሰብአዊ መብት ተሚጋቹ ለአዱስ አበባ ዘጋቢያችን ገልጸዋል።


# የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ

## የሥርጭት ሞገድ ለውጥ አድርጓል።

በዚሁ መሰረት ከአሁን ቦኋላ በ7485 KHZ በ41 ሜትር ባንድ እና በ9610 KHZ በ 31 ሜትር ባንድ ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።